አስተማሪ ታሪክ

ከመሰልክ እኛን ምሰል

አለበለዚያ ከሀገራጆችን ንቀል እንዲሉ

ማለት አለመሆን ባታ ላይ እራስህ ሁን ስትገኝ ነው የኛነታችን ማንም አይወስድምና

በስርቆት የተገኘ ሰው በዙርያው ተቀዋሚ ስላለ ራሱን ይመልሰዋል ከቀጠለ ተቃርኖ (እውነት)ውሸትን አገልጣ ትሰጣለችሀ

አለም ላይ ሁለት ተቃርኖ opposite force exist አሉ።

ያልሆንከው ነገር ሁሉ ሲኩብህ የሆነከውን ያንን ነገር አትርሳ"

አንድ ብርሃን ብሎ እራሱን ሚጠራ ነፍስ ነበር። ብርሀን መሆኑን በደንብ ያቀዋል። ሁሉም ብርሀን ብለው ይጠሩታል። ትንሹ ነብስ እራሱን ብርሀን እንደ ሆነ ይወቅ እንጂ ብርሀን ምን ማረግ እንዳለበት አያቅም። የብርሀን ጥቅሙን አልተረዳም ነበር። ታድያ ይሄ ትንሽ ነብስ ከቃላት በላይ መሆን የሚፈልገውን ነገር ለመራዳት የሚያስችለው ሁኔታ ውስጥ መገኘት ስላልቻለ ምንነቱን ከቃላት በላይ በድርጊት አያውቅም ነበር። ታድያ ይሄን ሁኔታ በመፈለግ በመሻት ይኖር ነበር። መሻቱ ትልቅ ነበርና ፈጣሪ አንድ ቀን ወደዚህ ትንሽ ነብስ ተጠግቶ " ትንሹ ብርሀን ሆይ መሻትህን አይቼ ተገርምያለው። መሻትህን ለማግኘት ምን ታረጋለህ? " አለው። ትንሹም ነብስ "ፈጣሪ ሆይ ሁሉንም አረጋለው" አለው። ፈጣሪም " ትንሹ ነብስ ሆይ አከባቢህን እስኪ ተመልከት አለው" አከባቢውን የተመለከተው ትንሹ ነብስ አንድ ትልቅ እውነታን ተረዳ። እከባቢው ሁሉ በብርሀን ነብሳት የተሞላ ነበር። ሁሉም ያበሩ ነበር። ፈጣሪም "ትንሹ ነብስ ሆይ ምን አየህ ?" አለው። ትንሹም ነብስ "በትልቅ ብርሀናት የተከበብኩ ብርሀን እንደሆንኩ!" አለው። ፈጣሪም " መሻትህን ታገኝ ዘንድ ብርሀንም ሚሰራውን ታውቅ ዘንድ የሆነ ምታረገው ነገር አለ" አለው ፈጣሪም። " ከነዚህ ብርሀናት ውስጥ አውጥቼ ወደ ጨለማ እልክሀለው" አለው ፈጣሪ ደግሞ። " ጨለማ ምንድነው አባት ሆይ?" አለ ትንሹ ነበስ። ፈጣሪም "ትንሹ የብርሀን ፀዳል ሆይ ጨለማማ አንት ያልሆንከው ያ ነገር ነው " አለው።

በዚህ ተስማምተው ትንሹ ብርሀን ወደ ጨላማ ግዛት ተላከ። ትንሹም ነበስ ለመጀመርያ ጊዜ ባልሆነው ነገር ሲከቡብ ፍርሀትን ተጋፈጠ። በብርሀናት ጥላ ስር ሆኖ የሚያበራው ያ ትንሽ ሻማ ተሸበረ። "አባቴ ሆይ ወዴት አለህ" ብሎ ተጣራ። ፈጣሪም " አይዞህ አለው። እራስህን ለማውቀ ብዙ ጥረሀልና ይሽው እራስህን ምታውቅበትን ሁኔታ አመጣውልህ።" አለው ፈጣሪ። ትንሹ ብርሀንም ግራ ተጋባ። " ፈጣሪ ሆይ ዙርያዬ ሁሉ በጨለማ ተውጧል። እንዴት ይሄ ለኔ ጥሩ ሁኔታ ሊሆን ይችላል?" አለ ትንሹ የብርሀን ወጋገን። "ልጄ ሆይ ያልሆንከው ነገር ሁሉ ሲኩብህ ያኔ የሆንከውን ያንን ነገር አስታውስ። ጨላማ ቢኩብህ ጨለማውን ትተተህ ብርሀንህን አስታውስ። ጨለማውን ከመርገም ጨለማው ላይ ብራ። ብርሀን የመሆንህ ቁም ነገር ጨላማ ላይ እንድትበራ ነውና። በብርሀናት ተኩብህ ሳለ ያኔ ምን እየሰራህ እንደሆነ አታውቅም። ምክንያቱም ብርሀን ብርሀን ላይ ቢያበራ ምንም የሚፈጠር ነገር የለምና። አሁን ግን የመፈጠርህ ትርጉሙ ብርሀን የመሆንህ ሚስጢር ተገልጦልሀልና ሄደህ በደንብ አብራ።" አለው። (from the book conversation with God)

የሁላችንም ጥንካሬ ያለው በተመቻቸው ስፍራ ሳይሆን ሁኔታዎች ፈር ሲለቁ ጨለማ ሲከበንና ህይወት መውጫ የሌላት መስላ ስታስጨንቀን በምንወስነው ውሳኔ ውስጥ ነው። የማንነታችን ትርጉም የሚለካው ነን ብለን የምናስበው ማንነታችን ፈተና ሲገጥመው በምንወስደው እርምጃ ነው። እራሳችንን የፍቅር ጥግ አርገን የምንይ ከሆነ የፍቅር ጥግ መሆናችንን የሚረጋገጠው ጥላቻ ግድ የሚሆንበት ቦታ ላይ የፍቅርን ፀዳል መልቀቅ ስንችል ነው። የይቅርታ ሰው መሆናችን የሚታወቀው ይቅርታ ለማረግ በሚያስቸግርበት ሁኔታ ላይ ይቅር ማለት ስንችል ነው።

ምክንያቱም ነን ብለን የምናስበው ሁሉ ያልሆነው ነገር ሲመጣ ይፈተናልና። እናም በምትፈተንበት ሰዓት የምታረገው ትልቁ ነገር ትልቁ መሸጋገርያህ ይሆናል።

ታድያ ፍቅር ስትሆን ጥላቻ መሀል ትሄዳለህ። ህይወት ስትሆን ሞት መሀል ትራመዳለህ። ሰላም ስትሆን ጦርነት መሀል እራስህን ታገኛለህ። ደግ ስትሆን ክፋት ይኩበሀል። እና ይሄ ሁሉ የሚሆነው ነኝ ብለህ የምታስበውን ብርሀን ነኝ ብለህ የምታስበውን ፍቅር ነኝ ብለህ የምታስበውን መልካምነት ታረጋግጥ ዘንድ ነው። " እኔ መልካም ሆኜ ሳለው ለምን መከራ በኔ ላይ ፀና" ብለህ ምታዝን ከሆነ አላማውን ስተሀል። ማንም ክፉ የለምና። ሁሉም ደግ ሁሉም ቸር ሁሉም ፍፁም ነውና። ነገር ግን አንዳንዱ ሁኔታው ሲናወጥ ማንነቱ መርሳቱ ነው። ስልጣን ፤ ገንዘብ፤ ረሀብ ፤ ጥጋብ ፤ ድህነት . . . ወዘተ ማንነትን የማስረሳት ችሎታ አላቸውና። ታድያ ሚሰርቅ ስታይ ሌባ ባለመሆንህ እራስህን እንደ ፃዲቅ አትቁጠር። ምክንያቱም የሌባው ቦታ ላይ ብትሆን እራስህ ያንን ነገር ላለማረግህ ምንም ዋስትና የለህምና። ስንዶች በተናገሩ ባወገዙት በጠሉት ነገር እራሳቸው ገብተውበት አይተናልና።

ፍጥረት ሁሉ ፍፁም መሆኑን ተረዳ። ፍፁም ያልሆነ ሁኔታ እንጂ ፍፁም ያልሆነ ሰው የለም። ሁሉም ሰው ክፍቶብህ ከታየህ ከመራገም ይልቅ ነኝ ብለህ ምታስበውን መልካምነት ሁን። ጥላቻ ሲኩብህ ነኝ ብለህ ምታስበውን ፍቅር ሁን። ይሄን መሆን ካልቻልክ ግን ሁሌም ቢሆን ማንነትህን ሳታውቅ ትኖራለህ። እራስን መካድ የፈጠረን መካድ ነው። ውብ እና ድንቅ ሆነህ ከተፈጠርክ ውብ ና ድንቅ ሆነህ መኖር ብቸኛው አማራጭህ ነው። ውብ ና ድንቅ ሆኖ የተፈጠረው ደግሞ አንተ ብቻ ሳትሆን ሁሉም ነውና መንገዱን የሳተ ሰው ሲጎዳህ ከመርገም ይልቅ ወደ ውብነቱ ወደ መልካምነቱ የሚመለስበትን ብርሀን አብራበት